# ለመሆኑ የከሰረው ማነው?

*በዳዊት ከበደ

አገሬን ከለቀቅኩ ድፍን አንድ ወር ሞላኝ፡፡ በኢትዮጵያ ምድር ዳግም እንዳትታይ የተፈረደባት አውራምባ ታይምስ ጋዜጣም ህትመቷ ከቆመ እነሆ አራት ቅዳሜዎች አለፉ፡፡ በሽመልስ ከማል የቦርድ ሊቀመንበርነት የሚመራው አዲስ ዘመን ግን ስድቡን አላቆመም፡፡ ‹‹የአውራምባ ታይምስ ሳምንታዊ ኮፒ ወደ 2000 ወርዶ ድርጅቱ ኪሳራ ውስጥ ነበር›› የሚል አዲስ ፕሮፖጋንዳ ጋዜጣውና ባለስልጣናቱ ማስተጋባት ጀምረዋል፡፡ የአራት ኪሎ ባለስልጣናት ‹‹የጋዜጣውን ትክክለኛ ኮፒ እዚያው አራት ኪሎ ከሚገኘው ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት አረጋግጠው የሰጡት መግለጫ ሊሆን ይችላል›› ብሎ የሚቀበል ሰው (የራሳቸው ደጋፊም እንኳን) ይኖራል ብዬ አላስብም፡፡ ምክንያቱም ከአንዳንድ የኢህአዴግ ደጋፊ ወዳጆቼ ያረጋገጥኩት ነገር እሱ ነውና፡፡ ደግሞስ ለዚህ ጉዳይ ሲባል ብቻ የኢህአዴግ አመራሮች ያልፈጠረባቸውን (ነገሮችን በጥሞና የመመርመርና የማመዛዘን) ባህሪ ዛሬ ከየት ያመጡታል? በዚህ ጉዳይ ላይ ከወዳጄ ተመስገን ደሳለኝ ጋር በስልክ ስናወራ ‹‹የመጨረሻውን የአውራምባ ዕትም የኮፒ መጠን የሚያረጋግጠው ደረሰኝ ለምን ከብርሀንና ሰላም አትወስድምና የምታደርገውን አታደርግም›› ስለው ‹‹እኔማ አውቀዋለሁ እኮ፤ማረጋገጥም አይጠበቅብኝም›› የሚል አጭር መልስ ነበር የሰጠኝ፡፡ አዎ! አጀንዳው የተረጋገጠ መረጃ በማቅረብና ባለማቅረብ የሚገታ እንዳልሆነ እነ ተመስገን ቀርቶ ማንም ዜጋ ጠንቅቆ የሚያውቀው ሐቅ ነው፡፡ ሌላው ቢቀር ይህንን ተራ አሉባልታ ‹‹ኤ.ኤፍ.ፒ›› ን ለመሳሰሉ አለም አቀፍ ሚዲያዎች በግልጽ የተናገሩት አቶ ሽመልስ ከማል የየሳምንቱን የኮፒ ብዛት የሚያረጋግጥ ሰነድ ከብርሀንና ሰላም ቢሮአቸው ድረስ በግዳጅ እንደሚያስመጡ የማያውቅ ጋዜጠኛ ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖራል ብዬ አልጠራጠርም፡፡ ያም ሆኖ ግን አሁንም ሰውዬው ሰነዱን ተመልክተው ሐቁን እንዲመሰክሩ አልወተውታቸውም፡፡ ምክንያቱም የሹመታቸው ቃለመሐላ ሐቅን መመስከር ሳይሆን የአለቆቻቸውን ስልጣን ሊያራዝም የሚችል ማንኛውም አይነት መስዋዕትነት መክፈል፣ ውሸት ማስተጋባት እንደ አስፈላጊነቱም መፈብረክ እንደሆነ ጠንቅቄ አውቃለሁና ውሸትን መተዳደሪያ ካደረጉ ሎሌዎች እንዲህ አይነቱ የህሊና ምስክርነት የምጠብቅ የዋህ አይደለሁም፡፡

አቶ ሽመልስ የሚያውቁት አንድ እውነት ልጨምር፤ በኢትዮጵያ የነጻ ፕሬስ ታሪክ ውስጥ የመንግስትን ዘረኛ አካሄድ፣ የመልካም አስተዳደር ችግር፣ የሰብአዊ መብት ጥሰት የሚቃወሙ፤ በአጠቃላይ የዜጎችን የልብ ትርታ የሚያስተጋቡ ጋዜጦች በኢትዮጵያ ምድር ላይ በኪሳራ ህትመታቸው ሲቆም መመልከት ብዙም የተለመደ አይደለም፡፡

በአንጻሩ ግን በሀሰት ምስክርነት ደዌ የሚሰቃዩ፣ የአገርን ሉአላዊነት የሚቃረን ኤዲቶሪያል ፖሊሲ የነበራቸው ጋዜጦች በኪሳራ ሲሽመደመዱ ተመልክተናል፡፡ ከነዚህ ጋዜጦች መካከል አንዱ በ1990 ዓ.ም ለጥቂት ሳምንታት ከታተመ በኋላ የከሰመው የአቶ ሽመልስ ከማል ኒሻን ጋዜጣ አንዱ ነው፡፡ በርካታ የነጻው ፕሬስ ቤተሰቦች እንደሚያውቁት በኤርትራና ኢትዮጵያ መካከል የነበረውን ኢፍትሃዊ የሁለትዮሽ ስምምነት ብሎም ኤርትራ ኢትዮጵያን በግፍ የመወረሯ እንቆቅልሽ አንገብግቧቸው አንድ አቋም ከያዙ የነጻው ፕሬስ አባላት በተቃራኒ አቶ ሽመልስ የኤርትራን ወረራ የሚያበረታታ ርዕሰ አንቀጽ በመጻፋቸው ምክንያት ጋዜጣቸው በአንባቢ እጦት ከገበያ መውጣቱን አውቃለሁ፡፡ ዛሬ ግን ያኔ የዋሉት ውለታ ታሳቢ ተደርጎ የአቶ በረከትና የአቶ መለስ ታማኝ ሎሌ ሊሆኑ ችለዋል፡፡ አዎ! እውነቱን እንነጋገር ከተባለ፣ የመክሰር ልምድ ያለው አሊያም የከሰረ ፖለቲካ አራማጅ ብቻ ነው - ስለኪሳራ የሚለፍፈው፡፡ አሁንም እውነት እውነቱን እንነጋገር ከተባለ ለአለቆቻቸው ጥቂት የፖለቲካ ትርፍ ሲባል በኪሳራ ሀዲድ ላይ ያሉት አቶ ሽመልስና መሰሎቻቸው ብቻ ናቸው፡፡ ኪሳራው ደግሞ ፖለቲካዊ ብቻ ሳይሆን ሞራላዊም ጭምር መሆኑ እጅግ ያሳዝናል፡፡ ሽመልስን ቀረብ ብሎ ላስተዋላቸው ውስጣቸው በአንድ መጥፎ መንፈስ መሞላቱን ለማረጋገጥ ጊዜ አይወስድበትም፡፡ በአገራችን ባህል ለአቅመ አዳም የደረሰ ወንድ በሰው ፊት እጁ የሚንቀጠቀጥ ከሆነ፤ ‹‹ከሰብአዊነት በወጣ መልኩ አንድ የሰራው ሀጢያት አለ ማለት ነው›› ተብሎ ግምት ይወሰዳል፡፡ ለምሳሌ የሆስቴስ አበራሽ ሀይላይ የቀድሞ ፍቅረኛ በግለሰቧ ላይ ያንን ሰቆቃ የፈጸመው ህይወቱ በአንድ መጥፎ መንፈስ በመወረሩ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል አያጠያይቅም፡፡ ምክንያቱም እርምጃው ስንመለከተው በሰው ልጅ ደረጃ የሚፈጸም አይደለም፡፡ ነገር ግን የአፈጻጸሙን ዘግናኝነት ትተን በቀድሞ ፍቅረኞቻቸው ላይ የመግደል ሙከራ ለማድረግ የሚያስችልን ነውረኛ ተነሳሽነት በማሳየት ረገድ አቶ ሽመልስና የአበራሽ የቀድሞ ፍቅረኛ እኩል ናቸው ወደሚለው ድምዳሜ እንድንቃረብ ያደርገናል፡፡ ምክንያቱም አቶ ሽመልስ በተልካሻ ቅናት ተነሳስተው የቀድሞ ፍቅረኛቸው በሞት ለማስቀጣት የሚችሉትን የሐሰት ማስረጃ የፈበረኩ ደካማ ናቸው፡፡ ሰውየው እንዲህ በማድረጋቸው ለሞራል መስዋዕትነቱ ያገኙት አጸፋዊ ትርፍ የሚኒስትር ዴኤታነት ‹‹ስልጣን›› ብቻ ነው፡፡ ለዚያውም የቀድሞ ፍቅረኛቸው ዝነኛ ተቃዋሚ በመሆናቸው፡፡ ወደ ሞራል ኪሳራው ኋላ ላይ እመለሳለሁ፡፡

ቀደም ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርኩት አገሬን ለቅቄ ከመውጣቴ ከቀናት በፊት በአይኔ የተመለከትኳቸው የቃለጉባኤ ሰነዶች፤ ከዚህ በፊት የተሰጠኝን ‹‹ምህረት›› እንዲሰረዝ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ይቅርታ ቦርዱ ከመንግስት ኮሚኒኬሽን ጽ/ቤት ኃላፊዎች ማብራሪያ ጠይቆ አቶ ሽመልስ ጋዜጣው በፍርድ ቤት በተያዘ ጉዳይ ላይ የተሳሳተ

ድምዳሜ እየሰጠ የዳኝነት ነጻነት በመጋፋት ላይ መሆኑን፣ በተለይ የጋዜጣው ባለቤት የአሸባሪዎች ተላላኪና በህዝቦች መካከል ግጭት እንዲነሳ ዘረኛ ቅስቀሳ እያካሄደ ይገኛል ሲሉ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ ሽመልስ እንደሚያስቡት ቢሆን ኖሮ በእኔና በአቶ መለስ መካከል ሽመልስ የሚባል አማርኛ ተናጋሪ አያስፈልግም ነበር፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ከአቶ መለስ ጋር ያለኝ የትውልድና የመንደር ቅርርብ ሽመልስን ሎሌ ለማድረግ ከበቂ በላይ ነበር፡፡ ነገር ግን በእንደዚህ አይነት ቅርቃር ውስጥ ለመኖር የነ ሽመልስ አይነት ህሊና ያስፈልጋል፡፡ ከቲተር እንዳያልፍ ተገድቦ፣ በህወሓት ሹማምንት የሚሰጥን ስልጣን ተማምኖ፤ ያቺን ‹‹ስልጣን›› አንድ እርከን ከፍ ለማድረግ ቤተሰቡን፣ ፍቅረኛውንና ሞራሉን የሚሰዋ ደካማ፤ ስለ ትርፍና ኪሳራ ለማውራት እንዴት ይቻለዋል? በእኔ እምነት በዚህ ምድር ላይ ለሰው ልጅ ትልቁ ኪሳራ የሞራል ኪሳራ ይመስለኛል፡፡ እኛ ደግሞ በሞራልም በፋይናንስም አልከሰርንም፡፡ ከተሰደድኩ ከሁለት ሳምንት በኋላ ባልደረባዬ አቤል አለማየሁ በፍትህ ጋዜጣ ላይ ካሰፈረው መጣጥፍ ውስጥ ቀጣዩን አንቀጽ በመጋበዝ ብሰናበታችሁስ? በነገራችን ላይ ይህቺ የአቤል ፓራግራፍ ፕሪንት አድርጌ በመኝታ ቤቴ ግድግዳ ላይ ለጥፌአታለሁ፡፡ በመጀመሪያው የስደት ምዕራፍ ላይ ያሉ ተስፋ አስቆራጭ ፈተናዎችን እያሰብኩ (ውጭ የምትኖሩ ወገኖቼ ይህችን የፈተና ወቅት ስላለፋችሁባት ታውቋታላችሁ) በፈተናዎቹ ሆድ ሲብሰኝ ቀና ብዬ በእነዚህ አረፍተ ነገሮች እጽናናለሁ፤ በአውራምባ ስታፍ መካከል የነበረውን የመግባባት የመናበብና በጋራ የመስራት የወጣትነት ቃል ኪዳን ምን እንደሚመስል ለመመስከር እነዚህ አረፍተ ነገሮች ዘላለማዊ ምስክሮች ናቸው፡-

‹‹እድሜ ለመቁጠር፣ አንድ ቅጣ ያጣ ባለሀብትን አጉልቶ ፍርፋሪ ለመልቀም፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለማፈራረስ እና ለመፈረካከስ፣ ሰውን ወንጅሎ ለማሳሰር ያዋልነው ገፅ እና የጨረስነው ቀለም ሳይኖር ከጨዋታው የግድ ስለወጣን ኩራት ይሰማናል፡፡ በሀፍረት ከመኖር 194ኛ ሳምንት መቀጨት የተሻለ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ አንገት የሚያስደፋ ስራ ለአንድም ቀን ሰርተናል ብለን ስለማናምን አጐንብሰን ከመሄድ ነፃ ነን፡፡ አውራምባ ታይምስ ብትቆምም የሞራል የበላይነታችን ሁሌም ከእኛ ጋር ነው፡፡››

ቸር እንሰንብት!

---

*ዳዊት ከበደ፣ የ2010፣ የሲ.ፒ.ጄ ዓለም አቀፍ የፕሬስ ነጻነት ተሸላሚ ሲሆን አገሩን ለቆ እስከተሰደደበት ጊዜ ድረስ የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ መስራችና ማኔጂንግ ኤዲተር ነበር:: ለአስተያየት davehadar@gmail.com/